የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፺፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 99
ADDIS ABABA, 3rd August ,2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፬/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ........ገጽ ፱ሺ፩፻፺

## CONTENT

Proclamation No. 974/2016

International Development Association Financing Agreement for the Small and Medium Enterprise Finance Project, Ratification Proclamation …………Page 9190

### አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፬/፪ሺ፰

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ ልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፵፬ ሚሊዮን ፰፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር( አንድ መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ ልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብስባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

### PROCLAMATION No. 974/2016

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, A Financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount not exceeding 144,800,000.00 SDR (one hundred forty four million and eight hundred thousand SDR) Special Drawing Rights for financing the Small and Medium Enterprise Finance Project, was singed in Addis Ababa on the 15th day of June, 2016.

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on 7th the day of July ,2016.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with of Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-



፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ለአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፋይናንስ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፬/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5793-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፵፬ ሚሊዮን ፰፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አርባ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation maybe cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Small and Medium Enterprise Finance Project, Ratification Proclamation No. 974/2016.

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Credit number 5793-ET signed in Addis Ababa on 15th June 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 144,800,000 SDR (One hundred forty four million and eight hundred thousand SDR) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the financing Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of August, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**